Wednesday, Dec 10, 2014

# ዓይኖቼን ክፈት

ንጉሥ ዳዊት *"ዓይኖቼን ክፈት ከሕግህም ተአምራትህን አያለሁ"* (መዝሙር 119፡18) ብሎ የጸለየውን ጸሎት ባሰብኩት ቁጥር እጅግ ያስደንቀኛል፡፡ትልቅ ጸሎት ነው ብዬ አስባለሁ፡፡አዎ መንፈስ ቅዱስ ዓይኖቻችንን ካልከፈተው በስተቀር፣መጽሐፍ ቅዱስን በጥልቀት ሚዳት ይከብደናል፡፡ለዚህ ነው በጸጋው ዙፋን ፊት በቂ ጊዜ ማሳለፍ የሚገባን፤ለዚህ ነው የመንፈስ ቅዱስ ርዳታ ያለማቋረጥ የሚያስፈልገን፡፡በግሌ እግዚአብሔር ዓይኖቻችንን እንዲያበራልን መማጸኑ፣መጮኹና ነፍስን ወደ ላይ ማንሳቱ ጥበብ ነው ብዬ አስባለሁ፤ *"ማስተዋልን ወዳጅ ብለህ ጥራት"* (ምሳሌ 7፡4) ተብሎ ተጽፎልንስ የለ ?

የጌታ መንፈስ ካልረዳንና ፍቺውን ካልገለጠልን በስተቀር፣ዕውቀታችን ወሱንና ግልብ ነው የሚሆነው፡፡ለዚህ ነው ንጉሥ ዳዊት *"የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ ነው፥ ዓይንንም ያበራል"*(መዝሙር 19፡8) ብሎ የተናገረው፡፡አዎ ቃሉ በመንፈስ ቅዱስ ሲፈታ፣ዓይናችንን ይከፍተዋል፣ማስተዋልም እንድንችል ያደርገናል፤ *"የቃልህ ፍቺ ያበራል፣ሕጻናትን አስተዋይ ያደርጋል"* (መዝሙር 119:130) ተብሎ እንደ ተጻፈ!

መንፈሳዊውን ዓለም ለማስተዋል፣የእግዚአብሔር መንፈስ እገዛ እጅግ ያስፈልጋል፡፡አለበለዚያ አንድ ርምጃ መሄድ አይቻልም፡፡የፈለገውን ያህል ብሩህ አእምሮ ያለን ሰዎች ብንሆን፣የሚያምን ትሑት ልብ ከሌለንና በጌታ መንፈስ ላይ ካልተደገፍን፣ከሐሳቡ ጋር እንተላለፋለን፣ሐሳቡን እንስታለን ብሎም የገባን ማስሎን አስረጅና አስተማሪ ሆነን ብዙዎችን ልናሳስትና ልናስት እንችላለን የሚል ግምት አለኝ፡፡

ሚገኝ ጥሩ ነው፤የቀለም ዕውቀት ጥሩ ነው፤ነገር ግን አሁን ዋና የሚያስፈልገን ጉዳይ የልብ ብርሃን (በእንግሊዝኛው ኢንሳይት)ነው፤የሚያስፈልገን ማለጥ ነው፤የሚያስፈልገን በሚከተዋል የሚገኝ ሚዳት ነው፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በክርስቶስ ያገኙትን ማንነትና በረከት ከኤፌሶን 1፡1-11 ድረስ አበክሮ ያስረዳቸዋል፡፡ከዚያም ይህንን ዕምቅ ሀብትና ሰማያዊ ብልጽግና በሚገባ እንዲያዩት ዓይናቸው ይበሩ ዘንድ፣የጥበብና የማለጥ መንፈስ እንዲሰጣቸው እንደሚጸልይ ነግሯቸዋል፡፡እንዲህ ብሎ ነበር የጸለየላቸው፦

*"የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የማለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ። ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለ ጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው"* (ኤፌሶን 1፡17-19)

ይህንን የጸሎት ሐሳብ ዘርዘር አድርጌ እንድጽፈው ይፈቀድልኝ፡፡እንዲህ ነበር ያላቸው፦

ከሱ ጋር በሚኖራችሁ የጠበቀ ጸሎትና የቃል ሕብረት(እርሱን በማወቅ)፣የጥበብንና የማለጥን መንፈስ ታገኛላችሁ፡፡የጥበብና የማለጥ መንፈስ ስታገኙና ሲበዛላችሁ፣ዓይኖቻችሁ ይበራሉ፤ዓይኖቻችሁ ይከፈታሉ፡፡ዓይኖቻችሁ ሲበሩና ሲከፈቱ ደግሞ

- ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን እንደጠራችሁ ይገባችኋል
- በቅዱሳን ዘንድ ያለውን የርስት ክብር ባለጠግነት ትረዳላችሁ
- ኢየሱስን ከሞት ያስነሣውን የኃይሉን ታላቅነት ታውቃላችሁ

ስለዚህ ወገኖቼ ዋናው የሚያስፈልገን የልባችን ዓይኖች መብራታቸው አይመስላችሁም ? ዓይን ሲበራ አስደናቂ ነው፤ቃሉ *"የዓይን ብርሃን ልብን ደስ ያሰኛል"* (ምሳሌ 15፡30)ይላልና፡፡አዎ ቃሉ ሲበራና የጌታችን ኢየሱስ ጌትነቱ፣አዳኝነቱ፣ሁሉን ቻይነቱ ሲበራልን፣የመጀመሪያው የሚያገኘን በረከት አእምሮን የሚያልፍ ደስታ ነው፡፡የምናገኘውን ሐሤትና ደስታ ደግሞ ማንኛውም

ምድራዊ ቋንቋ ሊገልጸው አይችልም፤ አእምሮን ያልፋልና፣ ልዩ ነውና፣ ሰማያዊ ነውና፣ ማለኮታዊ ነውና፣ ከላይ ነውና!!

በቀለ በላቸው(ዶ/ር)

beke_abay@yahoo.com

240-330-5004